# የወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ማንዋል

## መግቢያ

### አጠቃላይ

የሀገራችንን ኢኮኖሚ ለማሣደግ በመንግሥት ደረጃ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ሥትራቴጂዎች ተነድፈው ተግባራዊ በመደረግ መሆኑና ከእነዚህም ውስጥ ዋነኛው ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ሥትራቴጂ /Agricultural Development Lead Industrialization-ADLI/ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በኢንዱስትሪ የልማት ሥትራቴጂ ሠነድ ውስጥ ኢንዱስትሪው ግብርና በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር ሥር ከኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች ውስጥ የዘርፉን የልማት ፍጥነትና አቅጣጫን የሚወስነው የኤክስፖርት ኢንዱስትሪ /Export Lead Industrialization/ መሆኑ በዝርዝር ተጠቅሷል፡፡ በዚሁ መሰርትም የኤክስፖርት ኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ የማበረታታትና የመደገፍ ሥራ በመንግስት ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተካሄደ ይገኛል፡፡

የገቢው ዘርፍም የመንግሥት ሥትራቴጂያዊ ዓላማዎችንና ግቦችን በተለይም ለኢንቨስትምንትን፣ለግብርናንና ለወጪ ንግድን የተሰጠውን ልዩ ትኩረት ከማሣካት አንጻር ከፍተኛ የሆነ ኃላፊነት አለበት፡፡ አዲሱ የወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት ዘርፉ አሁን ያሉትንና ወደፊት የሚኖሩትን ተገልጋዮችን ለማርካት ስለሚያስችል ይህን ኃላፊነት ለመወጣት ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡ የሥራ ሂደቱን የመቀየር ዓላማም ለወጪ ንግድ አንድቅስቃሴ ቀናና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የሀገራችን የወጪ ምርቶች በቀላሉና በፍጥነት ወደ ውጭ እንዲላኩና ከወጪ አንፃርም ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግና በዚህ ረገድ ይታይ የነበረውን ከፍተኛ የሆነ የተገልጋይ እሮሮና እንግልት ለማስቀረት ነው፡፡ የዚህን አዲስ የአሰራር ሥርዓት/የሥራ ሂደት/ ትግበራ የተሣካና ውጤታማ ለማድረግ በማኑዋል መደገፍ በማስፈለጉ ይህ የአሠራር ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡፡

### የማንዋሉ ዓላማ

የዚህ ማኑዋል ዋና ዓላማ ለባለሥልጣኑ ሠራተኞች፣ ለላኪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት የወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም በማን፣ እንዴትና መቼ

እንደሚከናወን በማመልከት ወጥ፣ ፍትሃዊና ግልፅነትን የተላበሰ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎችም፡-

- የወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን ለመፈፀም ባለሙያዎች ሊከተሏቸው የሚገባቸውን የሥራ ደረጃዎችን በዝርዝር በማሣየት በሁሉም የጉምሩክ ጣቢያዎች ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣
- ባለሙያዎች በየዕለቱ ለሚያከናውኗቸው ሥራዎች አንድ ዓይነት መነሻና ማዕቀፍ እንዲኖራቸው በማድረግ የተጠያቂነት ሥርዓትን መዘርጋት፣
- ላኪዎች ማሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችንና ኃላፊነታቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ በማድረግ ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ማስቻል፣ እና
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የወጪ ዕቃዎችን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀምን በቀላሉ እንዲረዱት በማድረግ ቅንጅታዊ አሠራርን መፍጠር የሚሉት ናቸው፡፡

<u>የማኑዋሉ አደረጃጀት</u>

ይህ ማኑዋል ሰባት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን በመጀመሪው ክፍል ስለወጪ ዕቃ ትርጉም፣ የወጪ ዕቃ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የሥራ ሂደት ዓይነቶች፣ ዲክለራሲዮን የሚቀርብባቸውንና የማይቀርብባቸው ወጪ ዕቃዎች፣ ስለወጪ ዕቃ ዲክለራሲዮን ምንነት፣ የዲክለራሲዮን ደጋፊ ሰነዶች ምንነት እና ስለጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ተዳስሰዋል፡፡ በሁለተኛው ክፍል ስለዲክለራሲዮን ምዝገባና ትመና አስፈላጊነትና የአፈፃፀም ቅደም ተከተሎች፣ የዲክለራሲዮን ምዝገባ በማን፣ እንዴትና መቼ እንደሚሰራ እና ስለዲክለራሲዮን ደጋፊ ሰነዶች አቀራረብ ተገልጿል፡፡ በሦስተኛው ክፍል የሰነድ የማጣራት ሥራ ተብራርቶ የተገለፀ ሲሆን በአራተኛው፣ በአምስተኛው፣ በስድስተኛው እና በሰባተኛው ክፍሎች እንደቅደም ተከተላቸው ስለ መሐል ሀገር ዕቃ ፍተሻ ፣ ስለ መውጫ ጣቢያ ዕቃ ፍተሻ ፣ ስለ ዕቃ ከአገር መውጣት ማረጋገጥ እና ዲክለራሲዮን የማይቀርብባቸው ዕቃዎች ተመልክቷል፡፡

## ክፍል-1-

## <u>የወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም አጠቃላይ መግለጫ</u>

<u>(General Description)</u>

1.1 ወጪ ዕቃ ማለት ከኢትዮጵያ የግዛት ክልል የመጨረሻ መውጫ በሆነ የጉምሩክ ጣቢያ በኩል በሕጋዊ መንገድ የሚወጣ በጉምሩክ አዋጅ ለ"ዕቃ" የተሰጠ ትርጉምን የሚያሟላ ማለት ነው፡፡

1.2 የወጪ ዕቃ የጉምሩክ ሥነሥርአት አፈጻጸም የሥራ ሂደት ማለት አንድ ወደ ውጭ አገር የሚላክ ዕቃ መረጃው ወይም ሰነዱ ለጉምሩክ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከአገር መውጣቱ እስከ ሚረጋገጥ ድረስ ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑ ተግባራትን የሚያካትት ሂደት ሲሆን በዚህ ማኑዋል ውስጥ ዕቃው ወደ ውጭ አገር ከሚላክበት ዓላማ፣ ከሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎችና ከስራ ፍሰቱ መለያየት የተነሳ የሥራ ሂደቱ በሦስት ዘርፎች ወይም ገፅታዎች (Process versions) ተከፍሏል እነዚህም፡-

1.2.1 በ<u>መደበኛነት ከአገር የሚወጣ ዕቃ (Permanent Export</u>)

በዚህ ዘርፍ ሥር ወደ አገር የማይመለሱና በዘላቂነት ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የኤክስፖርት ዓይነቶች በሙሉ ይካተታሉ፣ እነዚህም፡-

- ቀጥታ/መደበኛ የንግድ ወጪ ዕቃዎች፣
- የውጭ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓቶች ተጠቃሚ የሆኑ ወጪ ዕቃዎች፣
- የግልና የቤት ቁሳቁሶች፣
- የናሙናና የስጦታ ዕቃዎች፣
- የጠረፍ ንግድ ወጪ ዕቃዎችና
- ሌሎች ተመልሰው የማይመጡ ወጪ ዕቃዎች ናቸው፡፡

1.2.2 <u>በጊዜያዊነት ከአገር የሚወጣ ዕቃ (Temporary Export</u>)

በዚህ ዘርፍ ስር ለተለየዩ ዓላማዎች በጊዜያዊነት ከአገር የሚወጡ ወጭ ዕቃዎች የሚካተቱ ሲሆን፣ እነዚህም፡-

- ለግንባታ ሥራዎች በጊዜያዊነት ከአገር የሚወጡ፣

- ለጥገና ወይም ለመሳሰሉት በጊዜያዊነት ከአገር የሚወጡ፣
- በቱሪስቶች አማካኝነተ በጊዜያዊነት ከአገር የሚወጡ፣
- ለንግድ ማስፋፊያ ሲባል በናሙና እና በኤግዚቢዜሽን መልክ በጊዜያዊነት ከአገር የሚወጡ እና
- ሌሎች ተመልሰው ለመምጣት ከአገር የሚወጡ ዕቃዎች ናቸው፡፡

### 1.2.3 <u>ተመልሶ ከአገር የሚወጣ ዕቃ</u> (Re-export)

ተመልሶ ከአገር የሚወጣ ዕቃ ማለት ለተያዩ ዓላማዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ገብቶ ከተወሰነ ጊዜ ቆይታ በኋላ ከሀገር የሚወጣ ዕቃ ማለት ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ ሥር የሚካተቱ ወጪ ዕቃዎች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የግንባታ ሥራዎች ለማከናወን በጊዜያዊነት ገብተው ተመልሰው የሚወጡ፣
- ለጥገና ማከናወኛነት በጊዜያዊነት የገቡና ሳይቀየሩ ተመልስው የሚወጡ፣
- ለጥገና ወይም ለመሳሰሉት ሥራዎች ገብተው ተጠግነው ወይም መጠነኛ ለውጥ ተደርጎባቸው ተመልሰው የሚወጡ፣
- በቱሪስቶች የገቡና ተመልሰው የሚወጡ፣
- ለንግድ ማስፋፊያ ሲባል በናሙና እና በኤግዚብሽን መልክ የገቡና ተመልሰው የሚወጡ፣
- የተከለከሉ በመሆናቸው ወይም ገደብ የተጣለባቸው በመሆናቸው ወይም ቀረጥና ታክስ በዝቶባቸው ወይም በቀረጥ ነፃ ሱቆችና በቀረጥ ነፃ ዞኖች ሳይሸጡ በመቅረታቸው ወይም በመሰል ምክንያቶች ከጉምሩክ ወደብ /መጋዘን/ ተመልሰው የሚወጡ ዕቃዎች ናቸው፡፡

## 1.3. <u>የጉምሩክ ዲክለራሲዩን</u>

የወጪ ዕቃ ዲክላራሲዮን ማለት የጉምሩክን የአውቶሜሽን ሲስተም በመጠቀም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ሰነድ ወይም Single Administrative Document (SAD) ማለት ነው፡፡

### 1.3.1 <u>ዲክለራሲዮን የሚቀርብባቸውና የማይቀርብባቸው ወጪ ዕቃዎች</u>

#### 1.3.1.1 <u>ዲክለራሲዮን የሚቀርብባቸው ወጭ ዕቃዎች</u>

ዲክለራሲዮን የሚቀርብበት ወጪ ዕቃ ማለት ማንኛውም በንግድም ሆነ በሌላ ምክንያት ከኢትዮጵያ ለመውጣት እንዲችል የጉምሩክ ዲክለራሲዮን በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ቀርቦበት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀምበት ዕቃ ማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረት በተራቁጥር 1.3.1.2. ላይ ከተዘረዘሩት ዕቃዎች ውጭ ያሉ ወጪ ዕቃዎች በሙሉ ዲክለራሲዮን ይቀርብባቸዋል ፡፡

#### 1.3.1.2 <u>ዲክለራሲዮን የማይቀርብበት ወጪ ዕቃ</u>

ዲክለራሲዮን የማይቀርብበት ወጪ ዕቃ ማለት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለመፈፀም ሲባል በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ለባለሥልጣኑ የጉምሩክ ዲክለራሲዮን የማይቀርብበት ዕቃ ማለት ነው፡፡ እነዚህም፡-

1. ዝርዝራቸው ከዚህ ማኑዋል አባሪ ሆኖ የተገለጸ እቃዎች ፣
2. የቤት እንስሳት/ውሻና ድመት የመሳሰሉ/ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሲቀርብና የንግድ መጠን የሌለው ሲሆን ፣
3. የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሻንጣዎችና እሽጎች፣
4. ወጪ ዕቃ የያዙ ኮንቴነሮች፣
5. የአውሮፕላን ወይም የመርከብ ውስጥ መገልገያዎች፣
6. ከአገር ውጭ ላለ የኢትዮጵያ ሰራዊት የሚላክ እቃ በመከላከያ ማጓጓዣ ከአገር ሲወጣ፣

እነዚህን እቃዎች ወደ ውጭ የሚልኩ የወጪ ዕቃ ዲክለራሲዮን የማይሞሉ ቢሆንም የዕቃ መግለጫ ለጉምሩክ ማቅረብ ኣለባቸው፡፡ በቀረበው መግለጫ መሰረት መረጃው በጉምሩክ ሰራተኛ አማካይነት በሲስተም ይመዘገባል፡፡ መንገደኛው በእጁ ይዞት የሚሄድ ከሆነ ለግልና ለቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃ መግለጫ እንዲቀርብ አይጠየቅም፡፡

1.4 የዲክለራሲዮን ደጋፊ ሠነድ ማለት የወጪ ዕቃን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለማስፈፀም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ከሚቀርበው ዲክለራሲዮን ጋር በአባሪነት የሚቀርብ እንደሁኔታው በባለሥልጣኑ ወይም በላኪው ተደራጅቶ የሚቀመጥ ወጪ ዕቃን በተመለከተ በሌላ ጉዳዩ በሚመለከተው መ/ቤት የተሰጠ ፈቃድ/ማስረጃ እና በዕቃው ባለቤት የሚቀርብ ተጨማሪ ሰነድን የሚያጠቃልል ነው፡፡

1.5 የጉምሩክ አውቶሜሽን ሲሰተም ማለት ወጪ ዕቃ ዲክሌር የሚደረግበት፣ የወጪ ዕቃ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀምበትና የጉምሩክ መረጃዎች ተሰባስበው የሚያዙበት በኮምፒዩተር የታገዘ የባለሥልጣኑ ሶፍትዌር ማለት ነው፡፡

## ክፍል -2-

## አዲሱ  የወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት ፍሰት (ሥዕላዊ መግለጫ) -To-Be



አይደለም

የሰነድ
ትክክለኛነት
ይረጋገጣል።

አዎ

ሰነዱ ትክክል ነው?



አዎ

ሰነዱ ተቀባይነት አግኝቶ

ከዚህ በላይ የሰፈረውን የሥራ ሂደት ሙሉ ዑደት ተከትለው የሚሰተናገዱ የጉምሩክ ዲክለራሲዮን የሚቀርብባቸው ወጪ ዕቃዎች ናቸው፡፡

2.1. <u>የዲክለራሲዮን ምዝገባና ትመና የሥራ ደረጃ</u> (Step-1)




ይህ የሥራ ደረጃ ከአገር የሚወጣው ዕቃ ዓይነት፣ የዕቃውን ባለቤት/ላኪ እንዲሁም ገዢውን የሚመለከቱና ሌሎች መረጃዎች በዲክለራሲዮን ላይ ተሞልተው በጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም የሚመዘገቡበትና በዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥና ታክስ መጠን የሚተመንበት የሥራ ደረጃ ነው፡፡

2.2. <u>የዲክለራሲዮን ምዝገባና ትመና ሥራ አስፈላጊነት</u> (Purpose)

የወጪ ዕቃ ዲክለራሲዮን ምዝገባና ትመና ሥራ የሚያስፈልገው፡-

- ወደ ውጭ ስለሚላከው ዕቃ ዝርዝር መረጃዎችን ለማሰባሰብ እና
- ወደ ውጭ አገር በሚላከው ዕቃ ላይ ሊከፍል የሚገባው የቀረጥና ታክስ መጠን ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ፡፡

2.3. <u>የዲክለራሲዮን ምዝገባና ትመና ሥራ ቅደም ተከተሎች</u> (Procedures)

የዲክለራሲዮን ምዝገባና ትመና ሥራ ተግባራት የሚከናወኑት ከዚህ በሚከተለው ቅደም ተከተል ነው፡-

1. ወደ ውጭ አገር ስለሚላከው ዕቃ ዝርዝር መረጃዎች በጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ውስጥ ባለው የዲክለራሲዮን ላይ ይገባሉ ፣

2. ወደ ሲስተም የገቡ መረጃዎች ትክክለኛነት ከተረጋገጠ በኂላ ሲስተሙ የተሞላውን ዲክለራሲዮን ይመዘግባል ::ይታዘዛል :
3. በዲክለራሲዮን ላይ የተመዘገቡ መረጃዎች ትክክልና የተሟሉ ሆነው ዲክለራሲዮን በሲስተሙ ተቀባይነት አግኝቶ ከተመዘገበ በኂላ ትመና ይካሄዳል፣
4. ተመዝግቦ የተተመነው ዲክለራሲዮን ከሲስተም ይታተማል ::

## 2.4. <u>የዲክለራሲዮን ምዝገባና ትመና ማከናወን</u>

### 2.4.1. <u>የወጪ ዕቃ ዲክለራሲዮን ለመመዝገብና ትመና ለማከናወን የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎች</u>

ዲክለራሲዮን ለመመዝገብና ትመና ለማከናወን የሚያስፈልግ ቅድመ-ሁኔታ :-

- ከባለሥልጣኑ ፈቃድ በማግኘት ከጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ጋር ቀጥታ ግንኙነት ማድረግ ነው ::

### 2.4.2. <u>የወጪ ዕቃ ዲክለራሲዮን መያዝ ያለበት መረጃ</u>

በእያንዳንዱ ዕቃ ዓይነት ግዴታ የሆኑ መረጃዎች በአውቶሜሽን ሲስተሙ ውስጥ አስቀድመው የሚገለፁ ስለሆነ የዲክለራሲዮን መዝጋቢው በዲክለራሲዮን ላይ ያሉ ሳጥኖች የሚጠይቁትን መረጃ በሙሉ ማስገባት አለበት፡፡ በሳጥኖቹ ውስጥ መሞላት ካለባቸው መረጃዎች ውስጥ:-

- የዕቃው ባለቤት ስምና አድራሻ (የታክስ ከፋይነት መለያ ቁጥር)፣
- የገዢው ስምና አድራሻ፣
- የዕቃው ዓይነት (የታሪፍ ቁጥር)፣
- የዕቃው መጠን/ብዛት፣
- የዕቃው ዋጋ፣
- ዕቃው የሚሄድበት ሀገር
- ዲክሌር የተደረገበት የጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ ፣
- የሚፈተሽበት መቅረጫ ወይም መውጫ ጣቢያ ፣
- ከአገር የሚወጣበት ቀን ፣
- ከአገር የሚወጣበት የመተላለፊያ መንገድ ይገኛሉ ::

2.4.3. <u>የወጪ ዕቃ ዲክለራሲዮን የሚቀርብለት የሥራ ክፍል</u>

ዲክለራሲዮን ከማይቀርብባቸው ዕቃዎች በስተቀር በማንኛውም ወደ ውጭ አገር በሚላክ ዕቃ ላይ ዲክለራሲዮን የሚቀርበው ለጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ነው፡፡

2.4.4. <u>የወጪ ዕቃ ዲክለራሲዮን ማቅረቢያ ዘዴ</u>

ዲክለራሲዮን ከማይቀርብባቸው ዕቃዎች በስተቀር ለማንኛውም ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ የጉምሩክ ዲክለራሲዮን የሚቀርበው በኤሌክትሮኒስ መንገድ ነው

2.4.5. <u>የወጪ ዕቃ ዲክለራሲዮን በጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ውስጥ የሚያስገባው ማን ነው?</u>

የወጪ ዕቃ ዲክለራሲዮን ምዝገባ በጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም የሚከናወነው ዕቃውን ወደ ውጭ አገር በሚልከው የዕቃው ባለቤት ወይም የዕቃው ባለቤት በወከለው ሰው አማካይነት ነው፡፡

2.4.6. <u>የዲክለራሲዮን መረጃን ወደ ጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም የሚያስገባው ሰው ያለው ኃላፊነት</u>

ወደ ጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም በገቡ መረጃዎች ትክክለኛነት እና ዲክሌር የተደረገው ወጪ ዕቃ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞበት ከሀገር መውጣቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ ከዕቃው ጋር በተያያዘ የሚኖሩ ሁኔታዎችን የመቆጣጠርና የመከታተል ኃላፊነት በዋናነት የዕቃው ባለቤት ሲሆን የዕቃው ባለቤትን ወክሎ ሥራውን ያከናወነ ሰውም ወደ ጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ለገባ መረጃና በዕቃው አፈፃፀም ላይ ለሚከሰት ችግር አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ስለዚህም የዕቃው ባለቤት ወይም ውክልና ወስዶ የሚሰራ ሰው ተገቢ የሆነ የሙያና የሥነ-ምግባር ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

2.4.7. <u>የዲክለራሲዮን ትመና (Assessment) ማከናወን</u>

ወደ ውጭ አገር በሚላክ ዕቃ ላይ ቀረጥና ታክስ የሚተመነው በዕቃው ባለቤት ወይም በዕቃው ባለቤት በተወከለ ሰው አማካይነት ነው፣ ትመና የሚያከናውነው ሰው ከጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ጋር ያለውን ቀጥተኛ (Online) ግንኙነት ተጠቅሞ ባለበት ቦታ ሆኖ ትመና ማድረግና ውጤቱንም ማተም ይችላል፡፡

2.4.8. <u>የዲክለራሲዮን አባሪ ሠነዶች የሚቀርቡበት የጉምሩክ መቅርጫ ጣቢያ</u>

የወጪ ዕቃ የዲክለራሲዮን አባሪ ሰነዶች ለተጨማሪ እይታና ለተመዘገበው ዲክለራሲዮን ተቀባይነት ለመስጠት እንዲቻል ዲክሌር ለተደረገበት የጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ መቅረብ አለባቸው፡፡

2.4.9 <u>ዲክሌር የሚደረግበት መቅረጫ ጣቢያ</u>

- የንግድ ዕቃ ከሆነ የላኪው ዋና ጽ/ቤት በሚገኝበት አካባቢ ባለ የጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ በኩል ብቻ ዲክሌር መደረግ አለበት ፣
- ተመልሶ ከአገር የሚወጣ ዕቃ ከሆነ ወደ አገር ውስጥ በገባበት መቅረጫ ጣቢያ በኩል ብቻ ዲክሌር መደረግ አለበት ፡፡
- ሌሎች ወጪ ዕቃዎችን ላኪው ወይም ወኪሉ በመረጠው መቅረጫ ጣቢያ ዲክሌር ማድረግ ይቻላል ፡፡

2.4.10. <u>የዲክለራሲዮን አባሪ ሠነዶች በማን ይቀርባሉ?</u>

የዲክለራሲዮን አባሪ ሰነዶች ለጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ የሚቀርቡት በዕቃው ባለቤት ወይም በሚወክለው ሰው አማካኝነት ነው፡፡

2.4.11. <u>የዲክለራሲዮን አባሪ ሠነዶች መቅረብ ያለባቸው ጊዜ</u>

የወጪ ዕቃ ዲክለራሲዮን አባሪ ሰነዶች ዲክለራሲዮን ሲስተም ውስጥ ተመዝግቦ ትመና ከተከናወነ ከ48 ሰዓታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ዲክሌር ለተደረገበት የጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ መቅረብ አለባቸው፡፡

2.4.12. <u>የዲክለራሲዮን አባሪ ሠነዶች አቀራረብ</u>

የዲክለራሲዮን አባሪ ሰነዶች ለጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ ሲቀርቡ

1. ዋና (Original) መሆን አለባቸው፣
2. የተሟሉ (Complete) መሆን አለባቸው፣
3. የሰጪው አካል/መ/ቤት ማረጋገጫ/ፊርማና ማህተም/ ያረፈባቸው መሆን አለባቸው፡፡

2.4.13. <u>የዲክለራሲዮን ምዝገባና ትመና ሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ</u>

የዲክለራሲን መረጃ ወደ ሲስተም በትክክል ከገባ የምዝገባና ትመና ሥራ ያለምንም መዘግየት/ወዲያውኑ ይጠናቀቃል፡፡

## 2.5 <u>የዲክለራሲዮን ምዝገባና ትመና ሥራ ፍሰት</u>




# ክፍል -3-

## <u>የሠነድ ትክክለኛነት ማጣራት የሥራ ደረጃ (Step-2)</u>



### 3.1. የሠነድ ትክክለኛነት የማጣራት ሥራ አስፈላጊነት (Purpose)

የሰነድ ትክክለኛነት የሚጣራው፡-

- ወደ ውጭ የሚላከው ዕቃ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎች የተሟሉለት መሆኑን ለማረጋገጥ፣
- ወደ ጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም የገባው መረጃ በትክክል የገባ ለመሆኑ ለማረጋገጥ፣ እና ዕቃው ከሀገር እንዲወጣ የተፈቀደ መሆኑን ለማረጋገጥ፡፡

### 3.2. የሠነድ ትክክለኛነት የማጣራት ሥራ ቅደም ተከተል (Procedures)

- ላኪው የሚያቀርባቸውን የዲክለራሲዮን ደጋፊ ሰነዶችን መቀበል፣
- የሰነዶችን ትክክለኛነትና መሟላት ማረጋገጥ፣
- ላኪው በሲስተም የመዘገበውን ከደጋፊ ሰነዶች ጋር ማመሳከር፣
- ልዩነት ከተገኘ እንዲስተካከል ሰነዶቹን ለላኪው/ወኪሉ መመለስ፣
- ልዩነት ካልተገኘ ሰነዶቹን ወደ ዶኪማ በመላክ ለቀጣይ ሥራ ዲክለራሲዩን ተቀባይነት ማግኘቱን በሲስተም መግለጽ፡፡

### 3.3 የሰነድ ትክክለኛነት የማጣራት ሥራ ቅድመሁኔታዎች

- ዲክለራሲዮን በጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ተመዝግቦ የተተመነ መሆን አለበት፣
- ከጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም የታተመ ዲክለራሲዮንና ኣባሪ ሰነዶች መቅረብ አለባቸው ፡፡

### 3.4. የሠነድ ትክክለኛነት የሚጣራው በማን ነው?

የሰነድ ትክክለኛነት የሚጣራው በጉምሩክ በተመደበው ሁለገብ ሠራተኛ (Case Worker) ነው፡፡

### 3.5. የሠነድ ትክክለኛነት እንዴት ይጣራል ?

የሰነድ ማጣራት ሥራ የሚከናወነው

- የቀረቡ ሰነዶች ዋና ቅጅ(Original) መሆናቸውን በማረጋገጥ፣

- የተሟሉ (የሚፈለጉ) ሰነዶች በሙሉ መቅረባቸውን በማረጋገጥ፣
- ሰነዶቹን የሰጠው አካል (ፈቃድ ሰጪ ወይም ተቆጣጣሪ) በፊርማና ማህተም ማረጋገጫ የሰጠባቸው መሆናቸውን በማየት እና
- ሲስተም ውስጥ ከተመዘገበው መረጃ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን በማረጋገጥ ነው፡፡

## 3.6. የሠነድ ትክክለኛነት የማጣራት ሥራ የሚጠናቀቅበት ጊዜ

የሰነድ ማጣራት ሥራ የሚጀመረው ሰነዶቹ ለጉምሩክ ሁለገብ ሠራተኛ በቀረቡበት ወቅት ሲሆን የሚጠናቀቀው ሰነዶቹ ከቀረቡበት ጊዜ አንስቶ ባሉ 3 ደቂቃዎች ጊዜ ውስጥ ነው ፡፡

## 3.7. የሠነድ ትክክለኛነት የማጣራት የሥራ ፍሰት



## ክፍል -4-

### በመሐል ሀገር የሚደረግ ፍተሻ የሥራ ደረጃ (Step-3)




### 4.1. በመሐል ሀገር የሚደረግ የፍተሻ ሥራ አስፈላጊነት (Purpose)

በመሀል አገር የዕቃ ፍተሸ የሚደረገው

- ላኪዎች በፈለጉበት ቦታ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ፣
- በመውጫ ጣቢያ ለመፈተሽ የማይመቹ ወይም ሊፈተሹ የማይገባ ዕቃዎችን ለመፈተሽ፣
- በመውጫ ጣቢያ የሚኖር መዘግየትን ለማስቀረት እና
- በመቅረጫ ጣቢያ በኩል ክትትል የሚደረግባቸውን ዕቃዎች ፈትሾ ማረጋገጥ ስለሚያስፈልግ ነው።

### 4.2. በመሀል አገር የሚደረግ የፍተሻ ሥራ ቅደም ተከተል (Procedures)

በዚህ የሥራ ደረጃ ያሉ ተግባራት ቅደም ተከተል ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

- ዕቃው በመሀል አገር እንዲፈተሽ የተጠየቀ እና የተፈቀደ መሆኑን ከሲስተም ማረጋገጥ ፣

- ሲስተም በመክፈት የስጋት ደረጃውን ማየት ፣
- የስጋት ደረጃው፡-

ሀ. አረንጓዴ ከሆነ፡

ዕቃው በቀጥታ ወደ መውጪያ ጣቢያ እንዲሄድ ይፈቀዳል፣

ለ. ሰማያዊ ከሆነ፡

ዕቃው በቀጥታ ወደ መውጪያ ጣቢያ እንዲሄድ ይፈቀዳል የሰነድ ምርመራ በቀጣይ ይከናወናል ፣

ሐ. ቢጫ ከሆነ፡

- ዕቃው ከሀገር ከመውጣቱ በፊት ሰነድ ምርመራ ይከናወናል ፣
- ሰነዱ ችግር ከሌለበት ዕቃው በቀጥታ ወደ መውጪያ ጣቢያ እንዲሄድ ይፈቀዳል ፣
- ሰነዱ ችግር ከተገኘበት ፍተሻ በሚከናወንበት ቦታ በመገኘት በዕቃው ላይ በማሙና(sample) አካለዊ ፍተሻ ይካሄዳል ፣
- የተፈተሸው ዕቃ ችግር ካለበት ለኢንፎርስመንት ይተላለፋል፣
- የተፈተሸው ዕቃ ችግር ከሌለበት በማሸግ በቀጥታ ወደ መውጪያ ጣቢያ እንዲሄድ ይፈቀዳል፣
- የፍተሻ ውጤት ሲስተም ውስጥ ይመዘገባል ፡፡

መ. ቀይ ከሆነ፡

- የዕቃው ፍተሻ በሚከናወንበት ቦታ መገኘት ፣
- ዕቃው ከሀገር ከመውጣቱ በፊት ሙሉ የሰነድ ምርመራ እና አካላዊ ዝርዝር የዕቃ ፍተሻ ይከናወናል፣
- የተፈተሸው ዕቃ ችግር ካለበት ለኢንፎርስመንት ይተላለፋል፣
- የተፈተሸው ዕቃ ችግር ከሌለበት በማሸግ በቀጥታ ወደ መውጪያ ጣቢያ እንዲሄድ ይፈቀዳል፣
- የፍተሻ ውጤቱ ሲስተም ውስጥ ይመዘገባል፡፡

## 4.3. <u>በመሀል አገር የዕቃ ፍተሻ ማከናወን</u>

### 4.3.1 <u>በመሀል አገር የሚከናወን ፍተሻ ቅድመ-ሁኔታዎች</u>

- በመሀል አገር እንዲፈተሽ አስቀድመሞ በሲስተም መጠየቅ አለበት ፣

- በመሀል አገር እንዲፈተሽ የተፈቀደ መሆን አለበት ፣
- ከጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም የታተመ ዲክለራሲዮን እና የዕቃ ዝርዝር (Packing list) መቅረብ አለበት፣
- በመቅረጫ ጣቢያ ሰነድ ማጣራት ተከናውኖ ዲክለራሲዮን ተቀባይነት ማግኘቱን የሚገልጽ መረጃ ሲስተም ውስጥ መገኘት አለበት።

4.3.2 <u>በመሀል አገር ፍተሻ የሚከናወንበት ዘዴ</u>

በመሀል አገር ፍተሻ የሚከናወነው፡-

- ከአውቶሜሽን ሲስተም ውስጥ የስጋት ደረጃውን በማየት፣
- እንደ ስጋት ደረጃው በመለየት የሰነድ ምርመራ በማከናወን
- የስጋት ደረጃው ቀይ ከሆነ ዝርዝር የዕቃ ፍተሻ በማድረግ፣
- በሲስተም የተገለፀውን hpacking list ጋር በማመሳከር ፣
- ዕቃው ችግር ከተገኘበት ወደ ኢንፎርስመንት በማስተላለፍ፣
- ዕቃው ችግር ካልተገኘበት በማሸግ ወደ መውጫ ጣቢያ እንዲሄድ በመፍቀድ እና
- የፍተሻ ውጤትን በጉምሩክ ሲስተም ውስጥ በመመዝገብ ነው።

4.3.3 <u>በመሀል አገር ፍተሻ የሚከናወነው በማን ነው?</u>

በመሀል አገር ፍተሻ የሚከናወነው በመቅረጫ ጣቢያ በሚገኝ የጉምሩክ ሁለገብ ሠራተኛ ይሆናል።

4.3.4 <u>በመሀል አገር ፍተሻ የሚከናወንበትና የሚጠናቀቅበት ጊዜ</u>

በመሀል አገር የሚከናወን ፍተሻ መከናወን ያለበት ዕቃው እና የዕቃ ዝርዝር/ packing list/ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን

የዕቃው የስጋት ደረጃው፡-

| | |
|---|---|
| አረንጓዴ ከሆነ | ወዲያዉኑ |
| ሰማያዊ ከሆነ | ወዲያዉኑ |
| ቢጫ ከሆነ | በ9 ደቂቃ |
| ቀይ ከሆነ | በ12 ሰዓት ጊዜ ውስጥ |

ይጠናቀቃል።

## 4.4. <u>በመሐል ሀገር የሚደረግ ፍተሻ የሥራ ፍሰት</u>




## ክፍል -5- <u>በመውጫ ጣቢያ የሚደረግ ፍተሻ የሥራ ደረጃ (Step-4)</u>




### 5.1. <u>በመውጫ ጣቢያ የሚደረግ ፍተሻ አስፈላጊነት (Purpose)</u>

በመውጫ ጣቢያ  የዕቃ ፍተሻ የሚደረገው

- ላኪዎች በመሀል አገር ፍተሻ በመጠበቅ እንዳይጉላሉ ለማድረግ ፣
- ከአገር እንዲወጣ ያልተፈቀደ ዕቃ እንዳይወጣ ለመከላከል ፣
- ላኪዎች ዲክሌር ያደረጉትን የዕቃ መጠንና ዓይነት ብቻ ከአገር ማውጣታቸውን ለማረጋገጥ ፣
- ህገወጥ ንግድን ለመከላከል እና

- የተፋጠነ አገልግሎት ለመስጠት ነው ።

## 5.2. <u>በመውጫ ጣቢያ የሚደረግ የፍተሻ ሥራ ቅደም ተከተል (Procedures)</u>

በዚህ የሥራ ደረጃ ያሉ ተግባራት ቅደም ተከተል ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡፡

- የመንገድ ወረቀትእና የዕቃ ዝርዝር ከአጓጓዡ መቀበል፣
- ዕቃው መውጫ ጣቢያ መድረሱን በማረጋገጥ የዕቃ ደርሷል መልዕክት ለሲስተም ማስተላለፍ እና የስጋት ደረጃ ከሲስተም ማየት፣
- የዕቃው የስጋት ደረጃ፡-

ሀ. አረንጓዴ ከሆነ፡

ዕቃው በቀጥታ ከአገር እንዲወጣ ይፈቀዳል፣

ለ. ሰማያዊ ከሆነ፡

ዕቃው በቀጥታ ከአገር እንዲወጣ ይፈቀዳል፣

ሐ. ቢጫ ከሆነ፡

- ዕቃው ከሀገር ከመውጣቱ በፊት በማሙና(sample) አካላዊ የዕቃ ፍተሻ ይከናወናል ፣
- የተፈተሸው ዕቃ ችግር ካለበት ለኢንፎርስመንት ይተላለፋል፣
- የተፈተሸው ዕቃ ችግር ከሌለበት ከአገር እንዲወጣ ይፈቀዳል፣
- የፍተሻ ውጤት ሲስተም ውስጥ ይመዘገባል ።

መ. ቀይ ከሆነ፡

- ዕቃው ከሀገር ከመውጣቱ በፊት አካላዊ ዝርዝር የዕቃ ፍተሻ ይከናወናል ፣
- የተፈተሸው ዕቃ ችግር ካለበት ለኢንፎርስመንት ይተላለፋል፣
- የተፈተሸው ዕቃ ችግር ከሌለበት ከአገር እንዲወጣ ይፈቀዳል፣
- የፍተሻ ውጤት ሲስተም ውስጥ ይመዘገባል ።

## 5.3. <u>በመውጫ ጣቢያ የሚከናወን ፍተሻ</u>

### 5.3.1 <u>በመውጫ ጣቢያ የሚከናወን ፍተሻ ቅድመ-ሁኔታዎች</u>

- ከጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም የታተመ ወይም በላኪው የተዘጋጀ የመንገድ ወረቀት እና Packing list በአጓጓዥ መቅረብ አለበት፣

- በመቅረጫ ጣቢያ ሰነድ ማጣራት ተከናውኖ ዲክለራሲዮን ተቀባይነት ማግኘቱን የሚገልጽ መረጃ ሲስተም ውስጥ መገኘት አለበት ፣
- ዲክሌር ሲደረግ በሚፈትሽው መውጫ ጣቢያ በኩል ከአገር እንደሚወጣ የተገለጸ መሆን አለበት ።

5.3.2 <u>በመውጫ ጣቢያ ፍተሻ የሚከናወንበት ዘዴ</u>

በመውጫ ጣቢያ ፍተሻ የሚከናወነው

- ከአውቶሜሽን ሲስተም ውስጥ የስጋት ደረጃውን በማየት፣
- ስጋት ደረጃው ቢጫ ከሆነ ናሙና(sample) ወስዶ የዕቃ ፈተሻ በማድረግ፣
- ቀይ ከሆነ ዝርዝር የዕቃ ፍተሻ በማድረግ፣
- በሲስተም የተገለፀውን በአጓጓዡ ከቀረበው የመንገድ ወረቀት እና ከpacking list ጋር በማመሳከር ፣
- ዕቃው ችግር ከተገኘበት ወደ ኢንፎርስመንት በማስተላለፍ፣
- ዕቃው ችግር ካልተገኘበት ወደ ውጭ እንዲወጣ በመፍቀድ እና
- የፍተሻ ውጤት በጉምሩክ ሲስተም በመመዝገብ ነው።

5.3.3 <u>በመውጫ ጣቢያ ፍተሻ በማን ይከናወናል ?</u>

በመውጫ ጣቢያ የመንገድ ወረቀት ከአጓጓዡ ከመቀበል ጀምሮ የዕቃ ፍተሻ አከናውኖ ውጤቱን ወደ ሲስተም እስከ ማስገባት ያለው ሥራ በጉምሩክ ሁለገብ ሠራተኛ ይከናወናል።

5.3.4 <u>በመውጫ ጣቢያ የሚከናወን ፍተሻ የሚከናወንበትና የሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ</u>

በመውጫ ጣቢያ የዕቃ ፍተሻ የሚከናወነው ዕቃው ፣ የመንገድ ወረቀት እና የእቃ ዝርዝር ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን የዕቃ ደርሷል መልዕክት ከማስተላለፍ አንስቶ ፍተሻን እስከ ማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ የስጋት ደረጃው፡-

| | |
|---|---|
| አረንጓዴ ከሆነ | በ2 ደቂቃ |
| ሰማያዊ ከሆነ | በ2 ደቂቃ |
| ቢጫ ከሆነ | በ6 ደቂቃ |
| ቀይ ከሆነ | በ12 ሰዓት ነው። |

## 5.4. በመውጫ ጣቢያ የሚደረግ ፍተሻ የሥራ ፍሰት




# ክፍል -6-

## *ዕቃ ከሀገር መውጣቱን የማረጋገጥ የሥራ ደረጃ* (Step-5)




*ዕቃ ከሀገር መውጣቱን የማረጋገጥ የሥራ ደረጃ ለጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ዲክሌር ተደርገው ወደ ውጭ ሀገር በሚላኩ ዕቃዎች ላይ ሁሉ የሚፈፀም ሲሆን ለጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ዲክሌር ተደርጎ ከሀገር ስለመውጣቱ ማረጋገጫ ያልተሰጠበት ዕቃ ከሀገር እንዳልወጣ ይቆጠራል፡፡*

### 6.1. *ዕቃ ከሀገር መውጣቱን የማረጋገጥ ሥራ አስፈላጊነት* (Purpose)

የዚህ የስራ ደረጃ አስፈላጊነት ከአገር ይወጣል ተብሎ ዲክሌር የተደረገ ዕቃ ዲክሌር በተደረገው መሠረት ከአገር መውጣን ለማረጋገጥ ነው፡፡

### 6.2. *ዕቃ ከሀገር መውጣቱን የማረጋገጥ ሥራ ቅደም ተከተል* (Procedures)

*ዕቃ ከሀገር መውጣቱን በማረጋገጥ የሥራ ደረጃ ላይ የሚከናወኑ ተግባራት ቅደም ተከተል ከዚህ እንደሚከለተው ነው፡፡*

1. ዕቃው ከአገር እንዲወጣ በመውጪያ ጣቢያ የተሰጠ የፈቃድ ሰነድን ከአጓጓዡ ወይም ከሲስተም መቀበል፣
2. ጭነቱ ከኢትዮጵ የግዛት ክልል መውጣቱን ማረጋገጥ፣
3. ዕቃው ከሀገር መውጣቱን የሚገልጽ ማረጋገጫ ወደ ጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ማስገባት፣
4. ከአጓጓዡ የተቀበለውን የመውጪያ ፈቃድ አያገለግልም /Void/ በማለት ፋይል አድርጎ ማስቀመጥ፣

## 6.3 ዕቃ ከአገር መውጣቱን የማረጋገጥ ሥራ ቅድመ ሁኔታ

ዕቃ ከአገር መውጣቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት አጓጓዥ ድርጅትም ሆነ የጉምሩክ ሁለገብ ሰራተኛ ዕቃው ከአገር እንዲወጣ በጉምሩክ መውጪያ ጣቢያ የተፈቀደ መሆኑን የሚገለጽ መረጃ ከጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ወይም ከአጓጓዡ በሰነድ አስቀድሞ ማግኘት አለበት፡፡

## 6.4. ዕቃ ከሀገር መውጣቱ የሚረጋገጠው በማን ነው ?

የዕቃ ከሀገር መውጣት የሚረጋገጠው ፡-

1. ዕቃው በአየር የሚጓጓዝ ከሆነ የአየር ማጓጓዣ ድርጅቱ ያረጋግጣል፣
2. ዕቃው በባቡር ወይም መኪና የሚወጣ ከሆነ በሀገሪቱ ግዛት የመጨረሻ መውጫ ጣቢያ ወይም በጎረቤት አገር ወደብ የሚገኝ የጉምሩክ ሁለገብ ሠራተኛ ያረጋገጣል፡፡

## 6.5. ዕቃው ከሀገር መውጣቱ እንዴት ይረጋገጣል ?

- ከጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ወይም ከዕቃው ጋር ከሚቀርብ ሰነድ ዕቃው ከአገር እንዲወጣ በጉምሩክ መውጫ ጣቢያ ፈቃድ የተሰጠው መሆኑን በማረጋገጥ ፣
- ዕቃው ከሀገር መውጣቱን በማየት እና
- መረጃውን በጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ውስጥ በመመዝገብ ዕቃ ከአገር መውጣቱ ይረጋገጣል፡፡

6.6. ***ዕቃ ከሀገር ለመውጣቱ ማረጋገጫ መስጫ ጊዜ***

*ዕቃ ከሀገር መውጣቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት አጓጓዥ ድርጅት(አየር መንገድ) ወይም ሁለገብ የጉምሩክ ሰራተኛ ማረጋገጫውን ዕቃው ከሀገር ከወጣ በኋላ ባሉ አራት ሰዓታት ጊዜ ውስጥ ወደ ጉምሩክ አውቶሜሽን ሲስተም ማስገባት አለበት፡፡*

6.7. ***ዕቃ ከአገር መውጣቱን የማረጋገጥ ሥራ የሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ***

*ዕቃ ከአገር መውጣቱን የማረጋገጥ ሥራ በ2 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ያጠናቀቃል ፡፡*

6.8. ***ዕቃው ከሀገር መውጣቱን የማረጋገጥ የሥራ ፍሰት***



## ክፍል-7-

## ዲክለራሲዮን የማይቀብባቸው ወጪ  ዕቃዎች አዲስ የሥራ ሂደት ፍሰት፣




በዚህ የሥራ ሂደት የሚስተናገዱት ዝርዝራቸው በተራቁጥር 1.3.1.2 ላይ የተገለጸወጪ ዕቃዎች ብቻ ናቸው ፡፡

7.1. <u>የሥራ ሂደቱ የመጀመሪያ ደረጃ (Step-1)</u>

የሥራ ሂደቱ ያለው አንድ ደረጃ ብቻ ነው፣ በዚህ የመጀመሪያ ደረጃ የዕቃ ፍተሻ ተከናውኖ በውጤቱ መሠረት እርምጃ ይወሰዳል፡፡

7.2. <u>የሥራ ደረጃው [illegible] (Purpose)</u>

የሥራ ደረጃው የሚያስፈልገው

- መንገደኞችንና ላኪዎችን በፍጥነት ለማስተናገድ እና
- የተከለከሉ ወይም ገደብ የተደረገባቸው ዕቃዎች ከአገር እንዳይወጡ ለመከላከል ነው ፡፡

### 7.3. የሥራ ደረጃው የአፈፃፀም ቅደም ተከተል (Procedures)

በዚህ የሥራ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ነው

1. በጉምሩክ ሁለገብ ሠራተኛ መንገደኛው ወይም ላኪው ያቀረበው ዕቃ ይፈተሻል፣
2. በህግ እና ደንብ የተከለከለ ዕቃ ከሆነ ለጣቢያው ኢንፎርስመንት ዕቃውና አምጪው ይተላልፋል፣
3. በህግ እና ደንብ ያልተከለከለ ሆኖ ወደ ውጭ ለመላክ ከሚፈቀድ መጠን/ብዛት በላይ ከሆነ አምጪው ዕቃውን ይዞ እንዲመለስ ይደረጋል፣
4. በህግ፣ደንብና መመሪያ ያልተከለከለና የተፈቀደ መጠን ከሆነ ዕቃው ከሀገር እንዲወጣ ይፈቀዳል፣

### 7.4. የሥራ ሂደቱ ቅድመ-ሁኔታዎች

በዚህ የሥራ ሂደት ለማስተናገድ የሚከተሉት ቅድመ-ሁኔታዎች ይጠየቃሉ

1. ዕቃው በህግ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ የተፈቀደ መሆን አለበት፣
2. የፈቃድ ሰጪ ወይም የተቆጣጣሪ አካላት ፈቃድ እንዲመጣለት የሚጠበቅ /ገደብ የተደረገበት ዕቃ መሆን የለበትም ፣
3. ለግል መገልገልገያነት በመንገደኛ እንዲያዙ ከሚፈቀዱ ዕቃዎች ውጭ ላሉት የዕቃውን ዓይነት ፣ መጠን/ብዛት ፣ ላኪውን እና የሚሄድበትን አገር የሚያሳይ በላኪው/በወኪሉ የተሞላ መግለጫ መቅረብ አለበት።

### 7.5. የሥራ ሂደቱ የሚጠናቀቅበት ጊዜ

በዚህ የሥራ ሂደት ለመስተናገድ የሚመጣ መንገደኛ ወይም ላኪ በ5 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱን አግኝቶ መሄድ አለበት።

### 7.6. የሥራሂደቱ  የሚከናወነው በማን ነው ?

በዚህ የሥራ ደረጃ ያሉ ተግባራት የሚከናወኑት በሁለገብ የጉምሩክ ሠራተኛ ነው።

### 7.7. የሥራ ሂደቱ ፍሰት



## 7.8- ዲክለራሲዮን ለማይቀርብበት ዕቃ በዕቃው ባለቤት ወይም በወኪሉ የሚሞላ የዕቃ መግለጫ ቅጽ

የቀረበበት ቀን------------------

ለ -------------------------------------- ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ ፡፡
ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ዕቃዎችን ወደ ----------------------- አገር ለአቶ/ወይዘሮ/ት-------------
ለመካክ ያቀረብኩ ስለሆነ አግልግሎት እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ ፡፡

| ተ/ቁ | የዕቃው ዓይነት | የዕቃው መለኪያ | የዕቃው ብዛት |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

የዕቃው ባለቤት ወይም የወኪል ስም -------------------------------- ፊርማ ------------------------
በጉምሩክ ሁለገብ ሰራተኛ የተሰጠ ውሳኔ መግለጫ ፡፡
-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------
ስም----------------------------- ፊርማ ---------------------------ቀን ------------------------

አባሪ አንድ

<u>ዲክለራሲዮን የማይቀርብባቸው ወጪ ዕቃዎች ዝርዝር</u>

| ተራ.ቁ. | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | <u>የግል መገልገያ ዕቃዎች</u> | | |
| 1.1 | የመንገደኛ የግል መገልገያ አልባሳት ፡ ጫማዎች እና የመሳሰሉ የንግድ መጠን የሌላቸው ። | ኪሎ/ቁጥር | በሙሉ |
| 1.2 | የመንገደኛ የግል መገልገያ መዋቢያ ዕቃዎች የንግድ መጠን የሌላቸው ። | በቁጥር | በሙሉ |
| 2 | <u>የስጦታ ዕቃዎች</u> | | |
| 2.1 | ከዕጸዋት የተሰሩ የባህል ዕቃዎችና አልባሳት ከእያንዳንዱ ዓይነት ። | በቁጥር | 5 |
| 2.2 | የደንና የዱር አራዊት ውጤቶች ከእያንዳንዱ ዓይነት ። | በቁጥር | 3 |
| 2.3 | <u>የዕጸዋትና የአዝርዕት ውጤቶች ለምግብነት የሚውሉ</u> | | |
| 2.3.1 | ቅመማ ቅመም ከእያንዳንዱ ዓይነት ። | በኪሎ | 1 |
| 2.3.2 | ሌሎች የዕጸዋትና የአዝርዕት ውጤቶች ከእያንዳንዱ ዓይነት ፡ ፡ | ኪሎ/ሊትር | 5 |
| 2.4 | <u>የእንሰሳት ውጤቶች</u> | | |
| 2.4.1 | የቆዳ አልባሳት ፡ጫማዎች፡ ቦርሳዎች፡ ከበሮዎች ወዘተ ከእያንዳንዱ ዓይነት ። | በቁጥር | 2 |
| 2.4.2 | ቅቤ፡ ማር፡ kንጣ ወዘተ ከእያንዳንዱ ዓይነት ። | በኪሎ | 5 |
| 2.5 | <u>የመዋቢያ ዕቃዎች</u> | | |
| 2.5.1 | ከእያንዳንዱ የመዋቢያ ዕቃ ዓይነት ። | በቁጥር | 2 |

| ተራ.ቁ. | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| 2.6 | የቤት ውስጥ መገልለያ ዕቃዎች | | |
| 2.6.1 | ከእያንዳንዱ የመገልለያ ዕቃ ዓይነት ፡፡ | በቁጥር | 2 |
| 2.7 | የግድግዳ ጌጣጌጦች | | |
| 2.7.1 | ከእያንዳንዱ የግድግዳ ጌጣጌጥ ዓይነት ፡፡ | በቁጥር | 4 |
| 2.8 | የአምልኮ ዕቃዎችና ቅዱሳን መጻህፍት | | |
| 2.8.1 | ቁርዓን እና መጽሃፍ ቅዱስ ፡፡ | በቁጥር | በሙሉ |
| 2.8.2 | ጽናጽል ፡ ጃንጥላ፡ ምርኩዝ ወዘተ ከእያንዳንዱ ዓይነት ፡፡ | በቁጥር | 3 |
| 2.9 | የህትመት ውጤቶች | | |
| 2.9.1 | ጋዜጦች ፡ መጽሃፍት እና መጽሄቶች ከእያንዳንዱ ዓይነት ፡፡<br>ደምጽ የተቀረጸባቸው ካሴቶች ከእያንዳንዱ ዓይነት ፡፡ | በቁጥር | 10 |
| 2.9.2 | ሌሎች ያልተከለከሉ ዕቃዎች ከእያንዳንዱ ዓይነት ፡፡ | በቁጥር | 10 |
| 2.10 | | በቁጥር | 1 |

ማሳሰቢያ

1 . ሁሉም ገደብ የተደረገባቸው ዕቃዎች በዚህ ዝርዝር ውስጥ አይካተቱም ፡
2 . ቡና ፡ ጫት ፡ ወርቅና የጌጣጌጥ ማዕድናት በዚህ ዝርዝር ውስጥ አይካተቱም ፡